# በኢትዮጵያ የንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት
# የኢንፎርሜሽንና ኮርፖሬት ኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት
## የሚዘጋጅ ወርሃዊ ዲጂታል መጽሔት

ሰኔ /2017 ዓ.ም

**ሐምሌ 5**
**በመትከል ማንሰራራት!**



**ከምርጫ ቦርድ መልማይ ኮሚቴ ሰብሳቢ እና አባላት ጋር በመሆን በምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ማዕረግ የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ማስተባበሪያ ማዕከል ኃላፊና የብልጽግና ፓርቲ ምክትል ፕሬዚዳንት አቶ አደም ፋራህ በተገኙበት ለተፎካካሪ ፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት የመልማይ ኮምቴ ሪፖርት መቅረቡን የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ሰብስብ አባፊራ አባጆቢር ገለጹ።**

**ፕሬዚዳንቱ በመልዕክታቸው ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች ተቀራርቦ በመስራት የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ከመገንባት ባለፈ የጋራ በሚያደርጉዋቸው ሀገራዊ አጀንዳዎች ላይ ተቀራርቦ ለመስራት የሚያደርጉት ዉይይት የሚደነቅ መሆኑና የመልማይ ኮሚቴ አባላትም ይህ አይነቱ አሰራር ተጠናክሮ እንዲቀጥል በርቱ እንላለን ብለዋል።**









## ማውጫ


የምርጫ ቦርድ መልማይ ኮሚቴ ————--1

የኢትዮጵያ የንግድና ኢንቨሥትመንት ፎረም –1

በመትከል ማንሰራራት ————-——--1

የማኔጅመንት ስራ አፈጻጸምና እቅድ ግምገማ-3

ከኦሮሚያ ቡና ገበሬዎች ህብረት ስራ ዩኒየን —4

ቴክኒክና ሙያ ስልጠና ውይይት——————5

ከሳፋሪኮም ጋር ውይይት——————————6

የአትዮጵያ የን/ኢንቨሥትመንት ፎረም———7

የጃፓን አሳካ ውይይየት ————————8

የአምባሳደር ዳባ ደበሌ አቀባበል—————-8

ከናይጀሪያ ምክር ቤት ጋር ውይይት————9

የአምባሳደር ለገሰ ገረመው ራት ግብዣ——-—9

የናይጀሪያ ቢዝነስ ፎረም——————-—-10

ከአምባሳደር ለገሰ ጋር ውይይት——————-10

የኢትዮ-ጃፓን ቢዝነስ ፎረም ———————-11

ሴቶች ስልጠና ሰጠ ———-——————12

ፋይናንስ ጉዳዮች ዙሪያ ውይይት ———-—-13

ማህበራት የምክር ቤቶች አባል መሆን———14

Africa in Motion ጋር ውይይት ————-15

የአፍሪካ ነጻ ንግድ ቀጠና ስልጠና—————15

የግሉ ዘርፍ ተሳትፎ በደን ልማት—————16

አድራሻ———————————————-18


### የኢትዮጵያ የንግድና ኢንቨሥትመንት ፎረም በሥካይላይት ሆቴል እየተካሄደ ነው።

በፎረሙም በውጭ ጉዳይ ሚኒሥቴር የመካከለኛው ምሥራቅ፣ የእስያ እና የፓሥፊክ ሀገራት ጉዳዮች ዳይሬክተር ጀነራል አምባሣደር ንጉስ ከበደ፣ የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የቦርድ አባላት፣ ከኢትዮጵያ ኢንቨሥትመንት ኮሚሽን እንዲሁም ከቻይና እና ከኢትዮጵያ የተውጣጡ የቢዝነስ ተቋማት ተወካዮች ተገኝተዋል።





በፎረሙም ኢትዮጵያ በተለይም ከምታካሂደው የኢኮኖሚ ሪፎርም አንጻር ለንግድና ኢንቨሥትመንት ምቹ መሆኗን ያነሱት አምባሣደር ንጉስ መንግስትም በግሉ ዘርፍ ያለው ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ የላቀ ውጤት እንዲያሥመዘግብ የተለያዩ ሥራዎችን እየሠራ መሆኑን ገልጸዋል።



የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤትም የግሉን ዘርፍ ለማንቀሣቀሥ የሚያደርገው ጥረትም የሚበረታታ መሆኑን ጠቅሠዋል።



የሻንግሀይ ሁጂኣን የባህልና ሚዲያ ኩባንያ ተወካይ ዝሀዎ ዚጂያንግ በበኩላቸው በሁለቱ ሀገራት መካከል ባለው የንግድና ኢንቨስትመንት ዙሪያ አብራርተዋል።

በኢትዮጵያ ኢንቨሥትመንት ኮሚሽን በኩል በኢትዮጵያ ባሉ ምቹ የኢንቨሥትመንት እድሎች እና መልካም አጋጣሚዎች ዙሪያ ማብራሪያ ተሠጥቷል።

## ሐምሌ 5 "በመትከል ማንሰራራት”



ዘንድሮ ለሰባተኛ ዙር "በመትከል ማንሰራራት” በሚል መሪ ቃል በሚካሄደውና የክቡር ጠቅላይ ሚንስትራችን ዶ/ር ዐብይ አሀመድ ሌጋሲ በሆነው የአረንጓዴ አሻራ የችግኝ ተከላ መርሐ ግብር ላይ ላለፉት ስድስት ተከታታይ ዓመታት ስንሳተፍ እንደነበረ ሁሉ፤

ዘንድሮም ሁሉም የምክር ቤታችን አባል  የንግድና ዘርፍ ማህበራት ም/ቤቶች፦ የክልል የወረዳና እና የከተማ አባል ም/ቤቶቻችሁን በማስተባበርና የንግዱን ማህበረሰብ ንቅናቄ በመፍጠር በአከባቢያቸሁ ከሚገኘውና ጉዳዩ በቀጥታ ከሚመለከተው የመንግስት መዋቅር ጋር በመቀናጀት በአገር አቀፍ ደረጃ በንግዱ ማህበረሰብ ስም ሐምሌ 05 ቀን 2017 ዓ.ም ችግኞችን በመትከል በአገራዊ የአረንጓዴ አሻራ መርሐ ግብር ላይ በመሳተፍ አሻራችሁን በማኖር የሚጠበቅባቸሁን ተቋማዊና ማህበራዊ ኃላፊነተቻችሁን እንድትወጡ አሳስባለሁ::

ሰብስብ አባፊራ አባጆቢር

የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት

**Bara kanas yeroo torbaffaaf Sagantaa Dhaabbata Dhaala Magariisaa mata duree "Haaromsa Dhaabbii" jedhuun gaggeeffamaa jiruu fi hambaa leegaasii Ministira Muummee keenya Dr Abiy Ahimed Ali.**

**Bara kana miseensonni mana maree keenyaa, waldaalee daldalaa fi seektara keenyaa, manneen maree miseensota naanoo godinaa fi magaalaa, hawaasa daldalaa keessan qindeessuun, caasaa mootummaa naannoo keessanii fi dhimmicha kallattiin ilaallatu waliin sochii uumuun, akkasumas Sagantaa Dhaala Magariisaa Biyyaalessaa irratti July 5, 2017, biqiltoota dhaabuun, maqaa hawaasa daldalaatiin akka hirmaattan isin gaafadha.**



## የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ም/ቤት ማኔጅመንት ስራ  አፈፃፀም እና በ2018 በጀት ዓመት ዕቅድ የትኩረት አቅጣጫ ላይ ተወያየ።

የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ም/ቤት የማኔጅመንት አባላት የም/ቤቱ ፕሬዚዳንት አቶ ሰብስብ አባፍራ አባጆብርና ም/ፕሬዚዳንቱ ዶ/ር ዓይናለም አባይነህ በተገኙበት በም/ቤቱ የ2017 በጀት ዓመት የዘጠኝ ወር  የስራ አፈፃፀም እና በ2018 በጀት ዓመት ዕቅድ የትኩረት አቅጣጫ ላይ ተወያየ።







Maanaajimentiin Mana Maree Daldalaafi Waldaalee Sekteraalee Itoophiyaa bakka Pirezidaantiin Mana Mari-chaa Obbo Sabsib Abbaafiraa Abbaajoobiriifi Itti Aanaan Pirezidaantii Dr. Ayinaalam.Abbaayinah argamanitti raawwii karooraa bara 2017 kan ji'oota saglan darbaniifi Ka'umsa karoora hojii bara 2018 irratti mari'achaa jira.







# የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ም/ቤት ከኦሮሚያ ቡና ገበሬዎች ህብረት ስራ ዩኒየን ጋር አብሮ መስራት በሚያስችሏቸው የጋራ ጉዳዮች ላይ ተወያየ፥

የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ም/ቤት ከኦሮሚያ ቡና ገበሬዎች ህብረት ስራ ዩኒየን ጋር አብሮ መስራት በሚያስችሏቸው የጋራ ጉዳዮች ላይ ተወያየ፥

በምክር ቤቱ ዋና ፀሐፊ ዶ/ር ቀነኒሳ ለሚ (ተባባሪ ፕሮፌሰር) የተመራው የማኔጅመንት ቡድን ከህበረት ስራ ዩኒየኑ የማኔጅመንት አባላት ጋር በተለይም በአቅም ግንባታ ስራዎች ላይ ያተኮረ ሰፊ ውይይት ያደረጉ ሲሆን ፤ የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ም/ቤት ተግባራዊ ባደረገው የለውጥ ስራ ለንግዱ ማህበረሰብ ከሚጠብቀው አለም አቀፍ ብርቱ ፉክክርና በአገር ኢኮኖሚ ዕድገት ውስጥ ሊኖረው ከሚገባው አበርክቶ አንፃር ሊያዘጋጀው በሚችል መልኩ አቅሙን ለመገንባት ልዩ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ መሆኑን ዶ/ር ቀነኒሳ አስርድተዋል። አሁን አገራችን የአለም ንግድ ድርጅት አባል ለመሆን ጫፍ ላይ በደረሰችበት ወቅት እና የአፍሪካ ነፃ የንግድ ቀጠና እንዲሁም የብሪክስ አባል በሆነችበት የአገራችን የንግዱ ማህበረሰብ ለሚጠብቀው ብርቱ ፉክክር እራሱን ማዘጋጀት አለበት ያሉት ዋና ፀሐፊው፤ ለዚህ ደግሞ ቢዚነሶች በቴክኖሎጂ ላይ ብቻ ኢንቨስት ማድረግ ብቻውን ተወዳዳሪ ለመሆን ስለማያስችል ቴክኖሎጂውን ተጠቅሞ ብቁ ተወዳዳሪ ሊያደርጋቸው በሚችል የሰው ኃይልም ላይ ትኩረት ሰጥተው መስራት እንዳለባቸው አስረድተዋል። ለዚህ ደግም የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ም/ቤት የስራ አመራር አካዳሚ ወቅቱን የዋጁ ስልጠናዎችን ስለሚሰጥ በዚህ ዕድል እንዲጠቀሙም አሳስበዋል።





የኦሮሚያ ቡና ገበሬዎች ህብረት ስራ ዩኒየን ዋና ስራ አስኪያጅ አቶ ደጀኔ ዳዲ በበኩላቸው ዩኒየኑ ከግማሽ ሚሊዮን አባላት በላይ ባላቸው 413 መሰረታዊ የህብረት ስራ ማህበራት የተደራጀና በአፍሪካ ትልቁ ዩኒየን እንዲሁም አለምአቀፍ ዕውቅና ያለው መሆኑን አንስተው፤ አሁን በአለም አቀፍ ደረጃ በስፔሻሊቲና ፕሪሚየም የቡና ሽያጭ ያለውን ተደራሽነትና ተወዳዳሪነቱን አጠናክሮ ይዞ ለመቀጠል የአቅም ግንባታ እጅጉን እንደሚያስፈልገው ገልፀዋል። ም/ቤቱ ዩኒየናችን አዲስ የለውጥ ጎዳና በጀመረበት ይህንን ሀሳብ ይዞ በመምጣቱ ደስተኛ ነው ያሉት አቶ ደጀኔ በተመቻቸልን ዕድል ለመጠቀም ዝግጁ ነንም ብለዋል።



የኦሮሚያ ቡና ገበሬዎች ህብረት ስራ ዩኒየን በአሜሪካና በአውሮፓ እንዲሁም በአውስተራሊያ ያለውን የገበያ ተደራሽነት በአፍሪካ ውስጥ የለውም ያሉት ዋና ስራ አስኪያጁ፤የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ም/ቤት ከአቻ የአፍሪካ ንግድ ም/ቤቶች ጋር በመነጋገር የገበያ ተደራሽነቱን እንዲያሰፋም ጠይቀዋል።





# በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና (TVET) ሥትራቴጂ ዙሪያ ውይይት ተካሄደ።

በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና (TVET) ሥትራቴጂ ዙሪያ ውይይት ተካሄደ።

በአዲስ አበባ ግረንድ ፓላስ ሆቴል የተካሄደው ውይይት የተዘጋጀው በኢፌዴሪ ሥራና ክህሎት ሚኒስቴር እንዲሁም በኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት እና GIZ -STEP 4 ድጋፍ ነው።

ውይይቱም የሥራና ክህሎት ሚኒስትር ደኤታ ዶክተር ተሻለ በሬቻ፣ የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ምክትል ዋና ጸሐፊ አቶ ጸደቀ ድጋፌን ጨምሮ ከጂአይዜድ STEP-4 ፣ ከግሉ ዘርፍ ባለድርሻ አካላትና ትላልቅ ኩባንያዎች የተውጣጡ ተወካዮች ተሣትፈዋል።

በኢትዮጵያ ያለው የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ውጤትን መሠረት ያደረገ፣ ከኢንዱስትሪው ጋር የተጣጣመ፣ ፍላጎትን መሠረት ያደረገና ውጤት ተኮር መሆን እንዳለበት ነው በውይይቱ የተነሣው።

የሥራና ክህሎት ሚኒስትር ደኤታ ዶክተር ተሻለ በሬቻ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ዘመኑ የሚፈልገውን እውቀት እና ክህሎት የያዙ ሠልጣኞችን ለማፍራትና ለኢንዱስትሪው ውጤታማነት አጋዥ የሚሆን ኃይል ለማፍራት ጥረት እየተደረገ መሆኑን ገልጸዋል።

የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ምክትል ዋና ጸሐፊ አቶ ጸደቀ ድጋፌ በበኩላቸው ፍላጎትን መሠረት ያደረገ፣ የመጪውን የቴክኒና ሙያ ሁኔታ ያገናዘበ፣ የግሉን ዘርፍ አሣታፊ ያደረገ እና ጥራትን መሠረት ያደረገ ሥራ እየተሠራ መሆኑን ጠቅሠው ምክር ቤቱም ዘርፉን የሚደግፍ ክፍል በማቋቋም ለመሥራት ጥረት እያደረገ መሆኑን አብራርተዋል።



የግሉ ዘርፍም ከሥርዓተ ትምህርት (Carriculum) ቀረጻ ጅምሮ በኢንዱስትሪ ትሥሥር፣ በሌሎችም አግባቦች የነቃ ተሣትፎ ማድረግ እንዳለበት ነው የተገለጸው።




ከሥልጠና ውጤታማነት ጋር በተያያዘ በተለይም በድህረ- ሥልጠና ሂደት ሠልጣኞች ያሉበትን ሁኔታ መዳሰስ አስፈላጊ ሲሆን ይህንን መነሻ በማድረግ በየጊዜው ውጤታማ ሥራ ለማከናወን ያግዛል ተብሏል።

በአዲሱ የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ መሠረት እየተዘጋጀ ያለው ሥትራቴጂ በተለይም ለTVET አስተዳደር ውጤታማነት የግሉ ዘርፍ ተሣትፎ ወሣኝነት ተነሥቷል።

በገበያው ተፈላጊ እውቀት እና ክህሎት ያለው ባለሙያ ለማፍራት ከ10 ዓመት የልማት እቅድ፣ ከሀገር በቀል ኢኮኖሚ ልማት እንዲሁም ከዲጂታላይዜሽንና ኢኖቬሽን፣ በተቋማት እና ኢንዱስትሪ ትሥሥር፣ በጥራት እና በሠርቲፊኬሽን አሠራር የተቃኘ ሥትራቴጂ ሊኖር እንደሚገባም ተገልጿል።





# የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ም/ቤት ከሳፋሪኮም ኢትዮጵያ ጋር አብሮ መስራት በሚያስችሏቸው የጋራ ጉዳዮች ላይ ተወያየ፥

የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ም/ቤት ከሳፋሪኮም ኢትዮጵያ ጋር አብሮ መስራት በሚያስችሏቸው የጋራ ጉዳዮች ላይ ተወያየ፥

በምክር ቤቱ ዋና ፀሐፊ ዶ/ር ቀነኒሳ ለሚ (ተባባሪ ፕሮፌሰር) የተመራው የማኔጅመንት ቡድን ከሳፋሪክም ኢትዮጵያ የማኔጅመንት አባላት ጋር በተለይም በአቅም ግንባታ ስራዎች ላይ ያተኮረ ሰፊ ውይይት ያደረጉ ሲሆን ፤ የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ም/ቤት ተግባራዊ ባደረገው የለውጥ ስራ ለንግዱ ማህበረሰብ ከሚጠብቀው አለም አቀፍ ብርቱ ፉክክርና በአገር ኢኮኖሚ ዕድገት ውስጥ ሊኖረው ከሚገባው አበርክቶ አንፃር ሊያዘጋጀው በሚችል መልኩ አቅሙን ለመገንባት ልዩ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ መሆኑን ዶ/ር ቀነኒሳ አስርድተዋል። አሁን አገራችን የአለም ንግድ ድርጅት አባል ለመሆን ጫፍ ላይ በደረሰችበት ወቅት እና የአፍሪካ ነፃ የንግድ ቀጠና እንዲሁም የብሪክስ አባል በሆነችበት የአገራችን የንግዱ ማህበረሰብ ለሚጠብቀው ብርቱ ፉክክር እራሱን ማዘጋጀት አለበት ያሉት ዋና ፀሐፊው፤ ለዚህ ደግሞ ቢዚነሶች በቴክኖሎጂ ላይ ብቻ ኢንቨስት ማድረግ ብቻውን ተወዳዳሪ ለመሆን ስለማያስችል ቴክኖሎጂውን ተጠቅሞ ብቁ ተወዳዳሪ ሊያደርጋቸው በሚችል የሰው ኃይልም ላይ ትኩረት ሰጥተው መስራት እንዳለባቸው አስረድተዋል። ለዚህ ደግም የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ም/ቤት የስራ አመራር አካዳሚ ወቅቱን የዋጁ ስልጠናዎችን ስለሚሰጥ በዚህ ዕድል እንዲጠቀሙም አሳስበዋል።

የሳፋሪኮም ኢትዮጵየዓ የውጭ ጉዳዮች ዋና ኃላፊ ዶ/ር አንዱአለም አድማሴ በበኩላቸው ኢትዮጵየዓ ለቴሌኮም ኦፐሬተሮች ክፍት ባደረገችው የኢኮኖሚ ምህዳር ውስጥ ተወዳድሮ በማሸነፍ አገልግሎት መስጠት ከጀመረ የሶስት ዓመት ተኩል ዕድሜ ያለው ድርጅታቸው ዛሬ ላይ ከአስር ሚሊዮን በላይ የሞባይል ተጠቃሚ ደንበኞች እንዳሉት ገልፀው ሳፋሪኮም በስድስት ድርጅቶች የቋቋመ አክሲዮን ማህበር ሲሆን በተለይም የአለም አቀፉ የቮዳፎን ኦፕሬተሮች አባል እነደመሆኑ አገለግሎቱ ፈጣንና ተደራሽ ነው ብለዋል። መንግስት ምንም እንኳን ምህዳሩን ክፍት ቢያደርግም ዛሬም የግሉ ዘርፍ መሰል አገልግሎት ከሚሰጡት መንግስታዊ ተቋማት ጋር እንዲወዳደሩ ከማድረግ አኳያ ማመቻቸት እንደሚቀረው ያነሱት ዶ/ር አንዱአለም የግሉ ዘርፍ ድምፅ የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ም/ቤት ከዚህ አንፃር ከፖሊሲ አውጪዎች ጋር መነጋገር አለበት ብለዋል።

በምክር ቤቱ የአመራር አካዳሚ ከሚሰጡ ስልጠናዎች ጋር በተያያዘ እንደ አገር ከፍተኛ ችግር እንዳለበት በሚታወቀውና የሳፋሪኮምም ችግር ነው ባሉት የማርኬቲንግ ክሎት ላይ ስልጠናው እጅግ እንደሚያስፈልጋቸው የጠቆሙት ኃላፊው የማህበራዊ ኃላፊነትን ከመወጣት አንፃርም ከም/ቤቱ ጋር ለመስራት ዝግጁ መሆናቸውን አረጋግጠዋል።













**የአትዮጵያ የንግድና ኢንቨሥትመንት ፎረም ኩባንያዎች ከሌሎች አቻዎቻቸው ጋር በጋራ ለመሥራት እድል የሚፈጥር መሆኑን የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የቦርድ አባል መጋቢ ሥርዓት ታየ ለታ ተናገሩ።**

በሥካይላይት ሆቴል በተካሄደው የኢትዮጵያ የንግድና ኢንቨሥትመንት ፎረም ላይ የተገኙት መጋቢ ሥርዓት ታየ የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ከውጭ ጉዳይ ሚኒሥቴር እና ከሌሎች አጋሮች ጋር በመተባበር መሠል የልምምድ ልውውጥ በማዘጋጀት እና በጋራ ለመሥራት እየተጋ መሆኑን አንሥተዋል።





የኢትዮጵያ እና የቻይና ኩባንያዎችም በተለያዩ የንግድና ኢንቨሥትመንት አማራጮች የሚያደርጓቸው የትብብር ሥራዎች ለጋራ ተጠቃሚነት የላቀ ሚና እንዳላቸውም በማጠቃለያ ንግግራቸው ላይ ጠቁመዋል።ከኢትዮጵያና ከቻይና ተውጣጡ ኩባንያዎችም በጋራ በሚሰሩባቸው ዘርፎች ዙሪያ የቢዝነስ ለቢዝነስ ውይይት አካሂደዋል።





**Waltajjiin Daldalaa fi Invastimantii Itiyoophiyaa Hoteela Iskaayilaayititti gaggeeffamaa jira.**

**Waltajjicharratti Ministeera Dhimma Alaatti Daayreektarri Olaanaa Dhimmoota Baha Giddu Galeessaa, Eeshiyaa fi Paasifikii Ambaasaaddar Akuse Kebede, miseensonni Boordii Mana Maree Daldalaa fi Industirii Itiyoophiyaa, bakka bu'oonni Komishinii Invastimantii Ityoophiyaa, akkasumas dhaabbileen daldalaa Chaayinaa fi Ityoophiyaa irraa argamanii jiru.**

**Itiyoophiyaan haaromsa diinagdee raawwachaa jirtu ilaalchisee iddoo daldalaa fi invastimantiif mijataa ta'uu cimsanii kan ibsan Ambaasaaddar Akuseen, mootummaan damee dhuunfaa keessattis sochii diinagdee dagaagsuuf hojjechaa jiraachuu ibsaniiru.**

**Manni Maree Daldalaa fi Industirii Itiyoophiyaa damee dhuunfaa sochoosuuf tattaaffii taasisaa jiru jajjabeessaa ta'uus eeraniiru.**

**Manni Maree Daldalaa fi Indaastirii Itiyoophiyaa Ministeera Dhimma Alaa fi michoota biroo waliin ta'uun gurmaa'ee waliin hojjechuun muuxannoo wal jijjiiruu fi waliin hojjechuuf hojjechaa akka jiru hirmaattonni waltajjichaa hubachiisaniiru.**

**Haasaa cufiinsaa isaanii keessatti walta'iinsi dhaabbileen Ityoophiyaa fi Chaayinaa filannoowwan daldalaa fi invastimantii adda addaa irratti taasifamaa jiru faayidaa waliiniitiif gahee guddaa akka qabu hubachiisaniiru. Dhaabbileen Ityoophiyaa fi Chaayinaa irraa dhufanis dameewwan waliin hojjetan irratti marii daldalaa gara daldalaatti gaggeessaniiru.**





## የኢትዮጵያ የንግድ ልዑካን ቡድን በጃፓን ኦሳካ ከተማ ከጃፓን ኩባንያዎች ጋር የአቻ ለአቻ ውይይት አካሄደ።

ኦሳካ ጃፓን – ጁን 26, 2025 – በኢትዮጵያ ንግድና የዘርፍ ምህበራት ምክር ቤት እና በጃፓን የኢትዮጵያ ኤንባሲ በጋራ ትብብር እንዲሁም







በኢፌዴሪ የንግድና ቀጣናው ትስስር ሚኒስቴር ፤ በኢንደስትሪ ፓርኮችና በዉጭ ጉዳይ ሚንስቴር ጠንካራ ተሳትፎ እየተካሄደ ያለው የጃፓን - ኦሳካ የንግድ ትርኢት አካል የሆነው የአቻ ለአቻ ዉይይት ዛሬ ተካሂዷል:

በውይይቱም፣ ተወካዮቹ በኢትዮጵያ ስላሉ የንግድና ኢንቨስትመንት እድሎች እንዲሁም በኢንዱስትሪ ልማት ዙርያ ሰፊ ዉይይት ያደረጉ ሲሆን በጋራ ሊተገበሩ በሚችሉ ስራዎች ዙሪያ መግባባት ላይ ተደርሷል ።



በውይይቱም በጃፓን የኢፌዴሪ ባለሙሉ ስልጣን አምባሳደር ዳባ ደበሌ፤ የኢትዮጵያ ንግድና የዘርፍ ምህበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ሰብስብ አባፊራ አባጆቢርን ጨምሮ ሌሎች ኃላፊዎችና ከሁለቱም አገራት የተወጣጡ የንግዱ ማኅበረሰብ አባላት ተገኝተዋል።

### በጃፓን-ቶክዮ ለሚገኘው የኢትዮጵያ የንግድ ልዑክ በኢፌዴሪ ባለ ሙሉ ስልጣን አምባሳዳር ዳባ ደበሌ እና በመላው የኤምባሲው ሰራተኞች ደማቅ የፕሮቶኮል አቀባበል እንደተደረገለት የኢትዮጵያ ንግድና የዘርፍ ምህበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ሰብስብ አባፊራ አባጆቢር ገለፁ።

ለተደረገው አቀባበል ምስጋናቸውን ያቀረቡት ፕሬዚዳንቱ ፤ ምክር ቤታችን ንግድና ኢንቨስትመንትን በማስተዋወቅ ረገድ ከኤምባሲው ጋር



የሚያከናውነውን ተግባር አጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል።

Jilli daldala Itiyoophiyaa simannaa ho'aa pirootokoolii Jaappaanitti Ambaasaaddara Itiyoophiyaa Dhaaba Dabalee fi hojjettoota isaaniitiin Tookiyootti taasifameef ::

Kabajamoo Ambaasaaddar Dhabaa Dabalee isin galateefana.





**የኢትዮጵያ ንግድና የዘርፍ ማህበራት ም/ቤት በኢትዮጵያና በናይጀሪያ መካከል ያለዉን የንግድና ኢንቨስትመንት ግንኙነት ማጠናከር በሚቻልበት ሁኔታ ላይ ከአቻዉ የናይጀሪያ የንግድ ኢንዱስትሪ ማዕድንና ግብርና ማህበራት ም/ቤት ጋር በናይጀሪያ አቡጃ ተወያይቷል።**

የኢትዮጵያ ንግድና የዘርፍ ማህበራት ም/ቤት በኢትዮጵያና በናይጀሪያ መካከል ያለዉን የንግድና ኢንቨስትመንት ግንኙነት ማጠናከር በሚቻልበት ሁኔታ ላይ ከአቻዉ የናይጀሪያ የንግድ ኢንዱስትሪ ማዕድንና ግብርና ማህበራት ም/ቤት ጋር በናይጀሪያ አቡጃ ተወያይቷል።









የኢትዮጵያ የንግድና የዘርፍ ማህበራት ም/ቤት ም/ል ፕሬዚዳንት ዶ/ር ዓይናለም አባይነህ እና ዋና ፀሐፊዉ ዶ/ር ቀነኒሳ ለሚ በናይጀሪያ አቡጃ በመገኘት ከናይጀሪያ የንግድ ኢንዱስትሪ ማዕድንና ግብርና ማህበራት ም/ቤት ጋር ባደረጉት ዉይይት የኢ/ን/ዘ/ማ/ም/ቤት ም/ል ፕሬዚዳንት ዶ/ር ዓይናለም አባይነህ የሁለቱን አገራት ታሪካዊ ግንኙነት በማንሳት አሁን በኢትዮጵያ በተፈጠረዉ ምቹ ሁኔታና ከተካሄዱ የኢኮኖሚ ፖሊሲዎች በተለይም በንግድና ማሻሻያ አኳያ የሁለቱ አገራት ግንኙነት ኢንቨስትመንት ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት አብራርተዋል።




የኢ/የን/ዘ/ማ/ም/ቤት ዋና ፀሐፊ ዶ/ር ቀነኒሳ ለሚ የም/ቤቱን ታሪካዊ ዳራና አሁን ያለበትን ነባራዊ ሁኔታ ያቀረቡ ሲሆን በተለይም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ተግባራዊ ባደረጋቸዉ ሪፎርሞች አሰራሩን በማዘመን በመንግስትና በግሉ ዘርፍ መካከል አገናኝ ድልድይ ሆኖ ከመስራት ባሻገር በአገሪቱ የኢኮኖሚ ዕድገት ዉስጥ የግሉ ዘርፍ ሚና ጉልህ ድርሻ ኢንዲኖረዉ የፖሊሲ ማሻሻያዎች እንዲደረጉ ከመንግስት ጋር ተቀራርቦ እየሰራ መሆኑን አስረድተዋል።

በሌላ መልኩ የኢትዮጵያ መንግስት ከወሰዳቸዉ የኢኮኖሚ ፖሊሲዎች ማሻሻያ አንፃር አሁን ያሉትን የኢንቨስትመንት አማራጮችንና አገሪቷ ያላትን ምቹ ሁኔታዎችን በዝርዝር በማቅረብ የናይጀሪያ ባለሀብቶችም በዚህ ምቹ ሁኔታ በመጠቀም በሁለቱ አገራት መካከል ያለዉን የንግድና ኢንቨስትመንት ግንኙነት እንዳያስፋፉና እንዲያጠናክሩ ጥሪያቸዉን አቅርበዋል ዶ/ር ቀነኒሳ።

## በናይጀሪያ አቡጃ የሚገኘዉ የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ም/ቤት ልዑክ በናይጀሪያ የኢትዮጵያ ባለሙሉ ስልጣን አምባሳደርና ልዩ መልዕክተኛ አምባሳደር ለገሰ ገረመዉ የእራት ግብዣ ተደርጎለታል።





ከእራት ግብዣዉ ጎን ለጎን የሁለቱን አገራት የንግድና ኢንቨስትመንት ለማጠናከር በሚያስችሉ ጉዳዮች ላይ ዉይይት የተካሄደ ሲሆን በእራት ግብዣዉና ዉይይቱ ላይ የቀድሞዉ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚ/ር አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝም ታድመዋል። የኢትዮጵያ የንግድና የዘርፍ ማህበራት ም/ቤት ልዑክም ለተደረገላት ግብዣና ዲፕሎማሲያዊ አቀባበል ላቅ ያለ ምስጋናዉን አቅርቧል።

Jiila Mana Maree Daldalaafi Waldaalee Sekterootaa gamauuf Ambassaaddara Garramawutiin affeerraan irbaataa kanarratti haala timantii cimsuun dan-

Itoophiyaa Naayijeeriaa, Abuujaatti ar-Itoophiyaa, Ambaasaaddar Laggasaa irbaataa taasifameefiira. Affeerraa walitti dhufeenya biyyota lamaaniifi qunnamtii daldalaafi invas-da'amurrattis mariin kan taasifame yoo ta'u, Ministirri Muummee Itoophiyaa duraanii Obbo Hayilamaariyam Dassaalenyis saganticharratti ar-gamaniiru. Jiilli Mana Maree Daldalaafii Waldaalee Sekteroota Itoophiyaas simannaafi affeerraa irbaataa taasifameefiif galateeffateera.



**በናይጄሪያ የንግድ ፣ ኢንዱስትሪ፣ማዕድንና ግብርና ምክር ቤት(NACCIMA)፣ በኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት እና በአቡጃ የኢፌዴሪ ኢምባሲ በጋራ ያዘጋጁት ኢትዮ- ናይጄሪያ የቢዝነስ ፎረም በአቡጃ ንግድና ኢንዱስትሪ ም/ቤት የስብሰባ አዳራሽ ተካሂዷል።**

በናይጄሪያ የንግድ ፣ ኢንዱስትሪ፣ማዕድንና ግብርና ምክር ቤት(NACCIMA)፣ በኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት እና በአቡጃ የኢፌዴሪ ኢምባሲ በጋራ ያዘጋጁት ኢትዮ- ናይጄሪያ የቢዝነስ ፎረም በአቡጃ ንግድና ኢንዱስትሪ ም/ቤት የስብሰባ አዳራሽ ተካሂዷል።





በፎረሙ ላይ ከናይጄሪያ በኩል የናይጄሪያ የንግድ ፣ ኢንዱስትሪ፣ማዕድንና ግብርና ምክር ቤት አባላት የሆኑት እና የተለያዩ የኢኮኖሚ ዘርፎችን ማለትም የግብርና፣ የማኑፋክቸርንግ፣ የማዕድን ልማትና የአገልግሎት ዘርፎችን የሚወክሉ ባለድርሻ አካላት በአካል እና በዲረ-ገፅ አማካኝነት የተሳተፉ ሲሆን በአገራችን በኩል የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ም/ቤት ም/ፕሬዝዳንት የሆኑት ዶ/ር ዓይናለም አባይነህ ፣ የም/ቤቱ ፀሐፊ የሆኑት ዶ/ር ቀነኒሳ ለሚ እና የሚሲዮኑ ባልደረቦች ተሳትፈዋል።



በፎረሙ ላይ የNACCIMA ፕሬዘዳንት ዶ/ር ኢንጂነር ጃኒ ኢብራሂም፣ የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ም/ቤት ም/ፕሬዝዳንት ዶ/ር ዓይናለም አባይነህ ፣ የም/ቤቱ ዋና ፀሐፊ ዶ/ር ቀነኒሳ ለሚ እና ም/ ሚሲዮን መሪ ክቡር አምባሳደር ኢሳያስ ጎታ ባስተላለፉት መልእክት በሁሉቱ አገሮች መካከል ስላለው ታሪካዊ ግንኙነት ፣በየአገሮቹ ስላሉትምቹ የቢዝነስና ኢንቨስትመንት ሁኔታዎችንና እምቅ አቅሞች እና እነዚህን አቅሞች ለጋራ ጥቅም እውን በማድረግ በሁለቱ አገሮች መካከል ያለውን የቢዝነስና የኢኮኖሚ ግንኙነት ወደ አዲስ ምዕራፍ ለማሸጋገር ርብርብ እንዲደረግ ጥሪ አስተላልፈዋል።የB2B ምክክሮችም ተደርገዋል።

የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ም/ቤት የስራ ሃላፊዎች በአቡጃ ቆይታቸው የንግድ ም/ቤቶች ስለተቋቋሙበት ዋነኛ ዓላማ ስለሆኑት ስለፖሊሲ አዲቮካሲ፣ ስለተቋም አስተዳደር፣ ስለአገልግሎት አሰጣጥ እና ስለፐቢሊክ ፕራይቬት ፓርትነርሺፕ የልምድ ልውውጥ ለማድረግ የሚያስችሉ ውይይቶችን ከNACCIMA የስራ ሃላፊዎች ጋር ያደረጉ ሲሆን በአቡጃ ውስጥ የመስክ ጉብኝቶችን አድርገዋል።

**የኢትዮጵያ የንግድና የዘርፍ ማህበራት ም/ቤት ም/ፕሬዚዳንት ዶ/ር ዓይናለም አባይነህ እና ዋና ፀሐፊ ዶ/ር ቀነኒሳ ለሚ ከ በናይጄሪያ ቆይታቸዉ ከናይጄሪያ የንግድ ማዕድን ኢንዱስትሪና ግብርና ም/ቤት እና ከናይጄሪያ የግሉ ዘርፍ ጋር የሁለቱን አገራት የንግድና ኢንቨስትመንት**





**ግንኙነትን ለማጠናከር የተደረገዉን ዉይይት ወደ ተጨባጭ ተግባር መቀየር በሚቻልበት ሁኔታ ላይ በዛሬዉ ዕለት በናይጄሪያ የኢትዮጵያ ባለሙሉ ስልጣን አምባሳደርና ልዩ መልዕክተኛ አምባሳደር ለገሰ ገረመዉ ጋር ፍሬያማ ዉይይት አድርገዋል።**

በሌላ በኩልም ከናይጄሪያ የንግድ ማዕድን ኢንዱስትሪና ግብርና ም/ቤት ጋር የልምድ ልዉዉጥ ለማድረግና የሁለቱን አገራት የንግድና ኢንቨስትመንት ግንኙነትን ለማጠናከርና ማሳለጥ በሚቻልበት ሁኔታ ላይ ለመምከር እንዲሁም የቢዝነስ ለቢዝነስ ግንኙነቶችን ለማመቻቸት ወደ ናይጄሪያ አቡጃ የተጓዘዉ የኢትዮጵያ የንግድና የዘርፍ ማህበራት ም/ቤት ልዑክ ከኢትዮጵያ ወደ ናይጄሪያ አበባ ስጋ ቡና እና ሰሊጥ ለመውሰድ ፍላጎት ካሳዩ የናይጄሪያ የግሉ ዘርፍ ጋር ዉጤታማ ወይይት አካሂዷል።





# የኢትዮ-ጃፓን ቢዝነስና ኢንቨስትመንት ፎረም በጃፓን ኦሳካ ከተማ ተካሄደ፤

እ.ኤ.አ ጁን 25 ቀን 2025 ኤምባሲው ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ያዘጋጀው የኢትዮጵያ-ጃፓን ቢዝነስና ኢንቨስትመንት ፎረም በጃፓኗ










ኦሳካ ከተማ ተካሄዷል። በፎረሙ ከሁለቱም አገራት የተለያዩ ካምፓኒዎች የተውጣጡ ከ75 በላይ የሚሆኑ ተሳታፊዎች፣ የመንግስት እና የንግዱ ዘርፍ የስራ ኃላፊዎች ተሳትፈዋል።

በዚህም በጃፓን የኢፌዴሪ ባለሙሉ ስልጣን አምባሳደርና ልዩ መልዕክተኛ ክቡር አምባሳደር ዳባ ደበሌ ንግግር ያደረጉ ሲሆን ኢትዮጵያና ጃፓን ረጅም ዘመን ያስቆጠረ ግንኙት ያላቸው መሆኑንን አውስተው ፎረሙ የሁለቱን አገራት የቢዝነስ እና ኢንቨስትመንት ግንኙነት ለማጠናከር ያለመ መሆኑን ጠቁመዋል። መንግስት በማክሮ ኢኮኖሚ ዘርፍ ያደረገው ሪፎርም ተከትሎ በአገራችን የተፈጠሩ የኢንቨስትመንትና ቢዝነስ ምቹ ሁኔታዎች የገለጹት ክቡር አምባሳደር የጃፓን ባለሀብቶች አገራችን ላይ ኢንቨስት ኢንዲያደርጉና በተለያዩ የቢዝነስ አማራጮች እንዲሳተፉ አበረታትተዋል።

የኦሳካ ከተማ ኢኮኖሚ ስትራቴጂ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል የሆኑት OKAMOTO Keiji ይህ ፎረም በማስተናገዳቸው ደስተኛ መሆናቸውን ገልፀው ኦሳካ






ከተማ ከኢትዮጵያ ጋር ታሪካዊ ቁርኝት ያላት መሆኑን፤ ለአብነትም በከተማዋ በሚካሄዱ የአትሌቲክስ ውድድሮች ኢትዮጵያዊያን አትሌቶች ድሎችን እንደሚያስመዘግቡ አውስተው ይህ ፎረም በቀጣይ በኦሳካ ከተማና በኢትዮጵያ መካከል የሚኖሩ ትብብሮችን እንደሚያሳድገው ያላቸውን እምነት ገልጸዋል።

የጃፓን የውጭ ንግድ ድርጅት (JETRO) የኦሳካ ቅርንጫፍ ዳይሬክተር NOZAWA Takuro በበኩላቸው የኢትዮጵያ መንግስት እና ኤምባሲው ለጃፓናውያን ካምፓኒዎች የቢዝነስ ዕድሎችን ለማመቻቸት እያደረጉ ያለውን ጥረት አድንቀዋል። በአገሪቱ የተደረጉ የኢኮኖሚ ሪፎርም ስራዎችና የፕራይቬታይዜሽን ተግባራትን ተጨማሪ የቢዝነስ አድል እንደሚፈጥሩ ዳይሬክተሩ አክለዋል። ቀጥሎም የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት አቶ ሰብስቤ አባፊራ ንግግር አድርገው አቅራቢዎችን ተጋብዘዋል።

የኢትዮጵያ ኢንድስትሪያል ፓርኮች ኮፖሬሽን ምክትል ስራ አስፈፃሚ አቶ ዘመን ጁነዲን የአገራችንን የኢንቨስትመንት አማራጮችና አስቻይ ሁኔታዎች አና ልዩ ኢኮኖሚ ዞኖች አሰመልክቶ ዝርዝር ገለፃ አቅርበዋል። በተመሳሳይ የአገራችን የቢዝነስና ከጃፓን ጋር ያለውን የንግድ ግንኙነት አስመልክቶ በንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር በኩል ሰፊ ገለፃ ተሰቷል።

በመጨረሻም በተሳታፊዎቹ በኩል ለተነሱ ጥያቄዎች በከፍተኛ ስራ ኃላፊዎች ምላሽ በመስጠት፣ የቢዝነስ ለቢዝነስ (B2B) ውይይት በማድረግ እና የአገራችንን ቡና አፈላል ሥነ-ስርአት ለታዳሚዎች በማስተዋወቅ ፎረሙ ተጠናቋል ሲሉ በፎረሙ ላይ የተሳተፉ የንግዱን ልዑክ በመምራት በጃፓን ኦሳካ የተገኙት የኢትዮጵያ የንግድና የዘርፍ ማህበራት ም/ቤት ፕሬዚዳንት ክቡር አቶ ሰብስብ አባፍራ አባጀብር በማህበራዊ የትስስር ገፃቸዉ አጋርተዋል።

# የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ከተለያዩ ማህበራት ለተውጣጡ በተለያዩ የቢዝነስ አማራጮች ለተሰማሩ ሴቶች ስልጠና ሰጠ

የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ከተለያዩ ማህበራት ለተውጣጡ በተለያዩ የቢዝነስ አማራጮች ለተሰማሩ ሴቶች ስልጠና እየሰጠ ነው።



ስልጠናው ሴቶች በፋይናንሻል ማኔጅመንት ዙርያ ያላቸውን ክህሎት ለማሳደግ ታሳቢ ያደረገ ነው።



የስልጠናውን መጀመር አስመልክቶ የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት የምክር ቤቱ ዋና ፀሐፊ ዶ/ር ቀነኒሳ ለሚ( ተባባሪ ፕሮፌሰር) ምክር ቤቱ አንጋፋ ተቋም መሆኑን ጠቁመው ፤እንደ ተቋም ከተሰጡን ተልዕኮዎች አንዱ የሴቶችን አቅም በተከታታይነት መገንባት ነው ብለዋል። በመሆኑም የሚሰጡ ስልጠናዎች አባሎቻችንና በተለያዩ ቢዝነሶች የተሰማሩ ሴቶች የንግድ ሳይንስ እውቀት ማሳደግ እንዲሁም ወጣቶችና አካል ጉዳተኞች በተሰሩ የተቋሙ የሪፎርም ስራዎች በስልጠና ብቁና ተጠቃሚ ማድረግ አንዱ የትኩረት አቅጣጫ መሆኑን ገልፀዋል።





ስለሆነም በንግድ ስራ የተሰማሩ ሁሉ የፋይናንስ ማኔጅመንትና የድጅታል እውቀታችሁን ማሳደግ፣ የሚሰጡ ስልጠናዎችን በስራ ቦታ መተግበርና የእውቀነት ሽግግር ማድረግ አስፈላጊ ነው ብለዋል።

ስልጠናው የአዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ መምህር እንዲሁም የፋይናንስ ባለሞያ በሆኑት በዶ/ር ሐውለት አህመድ እየተሠጠ ነው።



# የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ከተለያዩ ኩባንያዎች ተወካዮች ጋር በንግድ፣ ፋይናንስና ተያያዥ ጉዳዮች ዙሪያ ውይይት አካሄደ።

የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ከተለያዩ ኩባንያዎች ተወካዮች ጋር በንግድ፣ ፋይናንስና ተያያዥ ጉዳዮች ዙሪያ ውይይት አካሄደ።







ምክር ቤቱ Financial Barriers to Trade in Ethiopia: credit, collateral, Interest rate, and Foreign Exchange Volatility በሚል ርዕሥ በወጡ አዋጆችና አሠራሮች ዙሪያ ባንኮችን ጨምሮ የተለያዩ ተቋማት ተወካዮች በተገኙበት ነው የዴስክ ሪቪው (Desk Review) ውይይት ያካሄደው።

በውይይቱ ላይ ንግግር ያደረጉት የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ምክትል ዋና ጸሐፊ አቶ ጸደቀ ድጋፌ ምክር ቤቱ ከተሠጡት ኃላፊነቶች አንዱና ዋነኛው የምርምርና አድቮኬሲ መሆኑን በማንሣት በዚህም በፋይንሥ ዘርፉ እና የንግድ እንቅስቃሴው ምቹ ሁኔታ ዙሪያ የምርምርና አድቮኬሲ ሥራዎች ትኩረት እንደተሰጣቸው ገልጸዋል።

የምክር ቤቱ የሪሰርች እና አድቮኬሲ ቡድን መሪ አቶ ታከለ አየለ በተለይም ከወጡ አዋጆችና አሠራሮች ጋር በተያያዘ ምክር ቤቱ ያካሄደውን ዳሰሳ አቅርበዋል።



በዚህም ከፋይናንስ አቅርቦት፣ ማሥያዣ እንዲሁም የውጭ ምንዛሬ፣ ብድር አሠጣጥ፣ ማስያዣ (collateral)፣ የወለድ ምጣኔ፣ በብድርና ቁጠባ ተቋማት እንዲሁም በወጭ እና ገቢ ንግድ ዙሪያ የሚያጋጥሙ ችግሮችን እንዲሁም ያሉትን መልካም አጋጣሚዎችና ምቹ ሁኔታዎች በውይይቱ ተዳሰዋል።



ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን ተክቶ መጠቀም፣ ከብድር አቅርቦት፣ ለአነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች የተሻለ የፋይናንሥ አቅርቦት ማሟላትና ከባንኮች አሠራር ጋር የተጣጣመ መሆን ተደርጓል።

እንዲኖር፣ በፋይናንስ ጥያቄ በኩል አሥፈላጊ መረጃዎችን እንዳለበትና በመሣሠሉ ሀሣቦች ዙሪያ ሠፊ ውይይት

በምክር ቤቱም በተነሱና የንግድ ሥራውን የተሣለጠ ማድረግ የሚያስችሉ የጥናትና የአድቮኬሲ ሥራዎች በተጠናከረ መልኩ እንደሚከናወኑ ተጠቁሟል።

በውይይቱም፣ ባንኮች፣ ላኪዎች፣ የሴቶች ማኅበራት፣ የአነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ተወካዮች እንዲሁም የሌሎች ኩባንያዎች ተወካዮች ተገኝተዋል።



# ማህበራት የምክር ቤቶች አባል መሆን ዘርፈ ብዙ ጥቅም ያለው መሆኑን የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ዋና ጸሐፊ ዶክተር ቀነኒሳ ለሚ (ተባባሪ ፕሮፌሰር) ገለፁ።

ማህበራት የምክር ቤቶች አባል መሆን ዘርፈ ብዙ ጥቅም ያለው መሆኑን የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ዋና ጸሐፊ ዶክተር ቀነኒሳ ለሚ (ተባባሪ ፕሮፌሰር) ገለፁ።



ምክር ቤቱ ሪፎርም ካደረገ ጀምሮ በሴቶች የሚመሩ ቢዝነሶች የአቅም ግንባታ ላይ ትኩረት አድርጎ እየሰራ መሆኑን ገልፀዋል።



ይህንን የተናገሩት ከተለያዩ ማህበራት በፋይናንሻል ማኔጅመንትና በዲጅታል ማርኬቲንግ ዙሪያ ሲሰጥ የነበረው ስልጠና መጠናቀቁን አስመልክቶ ባደረጉት ንግግር ነው ፡፡ የተሰጠው ስልጠና በዘርፉ ላይ ያላቸውን እውቀት እና ክህሎት እንደሚያሳድግላቸው ሰልጣኞች ገልፀዋል። በስልጠናው ማጠናቀቂያ ላይም ከሰልጣኞች ለተነሱላቸው ጥያቄዎች ማብራርያ ሰጥተዋል ።በስልጠናዉ ማጠናቀቂያ ለሰልጣኞች የምስክር ወረቀት ተሰጥቷል።

Waldaaleen daldaltootaafi Sekteraalee Omishaafi kenniinsa tajaajila gara garaa irratti bobba'an miseensa Mana Maree Daldalaafi Waldaalee Sekteraalee ta'uun faayidaa hunda galeessa ta'e akka argatan gargaaraa jedhani Barreessaan Olaanaa Mana Maree Daldalaafi Waldaalee Sekteroota Itoophiyaa Dr.Qananiisaa Lammii ergaa xumura leenjii ijaarsa dandeettii dubartoota Biizinasii adda addaa gaggeessaniif kennamerratti.





## የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ም/ቤት Africa in Motion ከተባለ ድርጅት ጋር አብሮ መስራት በሚችሉበት ሁኔታ ላይ ተወያይቷል።

**የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ም/ቤት Africa in Motion ከተባለ ድርጅት ጋር አብሮ መስራት በሚችሉበት ሁኔታ ላይ ተወያይቷል።**



የኢትዮጵያ የንግድና የዘርፍ ማህበራት ም/ቤት የንግዱን ማህበረሰብ አቅም ከመገንባት ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት እየሰራ መሆኑን የም/ቤቱ ዋና ፀሐፊ ዶ/ር ቀነኒሳጨለሚ(ተባባሪ ፕሮፌሰር) በማስረዳትበተለይም በሴቶች ወጣቶችና አካል ጉዳተኞች የሚንቀሳቀሱ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞችን ከማብቃት አንፃር ልዩ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ መሆኑን ገልፀዋል።



አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ለስራ ዕድል ፈጠራና ለአገር ኢኮኖሚ ዕድገት እያበረከቱ ካሉት አስተዋፅኦ አንፃር ተገቢዉ ትኩረት እንዳልተሰጣቸዉ ያነሱት ዶ/ር ቀነኒሳ የኢትዮጵያ የንግድና የዘርፍ ማህበራት ም/ቤት እነዚህ ተቋማት በአገሪቱ እንደ አዲስ በተጀመረዉ የካፒታል ገበያ ዉስጥ ተገቢዉን ድርሻ እንዲኖራቸዉ ለማስቻል እየሰራ ነዉ ብለዋል። ስለሆነም Africa in Motion ሴት ስራ ፈጣሪዎችን በሚያበረታታበት Equal Tarade Alliance ቀተሰኘዉ ፕሮግራሙ ከም/ቤቱ ዓላማ ጋር የሚጣጣም በመሆኑ አብሮ ለመስራት ምቹ ሁኔታ መኖሩን አብራርተዋል።



የAfrica in Motion ዳይሬክተር ሚስተር ማክስ ኮፊ በበኩላቸዉ የድርጅታቸዉ ተልዕኮ ከኢትዮጵያ የንግድና የዘርፍ ማህበራት ም/ቤት ተልዕኮጨጋር እጅጉን የሚጣጣምና በዋና ዋና የም/ቤቱ ዓላማዎችና ተልዕኮዎች በአቅም ግንባታ ስልጠና በፖሊሲና አድቮኬሲ ላይ በጋራ ለመስራት ፍላጎት እንዳላቸዉ አሳዉቀዋል።

## የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት በአፍሪካ ነጻ የንግድ ቀጣና ሥምምነት ትግበራ ዙሪያ ለቢዝነስ ተቋማት ተወካዮች የግንዛቤ ማሥጨበጫ ሥልጠና ሰጠ።





ምክር ቤቱ ከGIZ አፍሪካ ህብረት የሥምምነቱ ድጋፍ ቡድን እንዲሁም ከንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በተዘጋጀው በዚህ የሥልጠና ፕሮግራም ከአነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች እሥከ ትላልቅ ኩባንያዎች ተወካዮች ተሣታፊ ናቸው።



ሥልጠናውም በዋናነት በኢትዮጵያ ታሪፍ ኦፈር፣ የኢንቨሥትመንት ፕሮቶኮልና በውድድር ፖሊሲ ፕሮቶኮል ዙሪያ ያተኮረ ነው።

በሥልጠናው ላይ የተገኙት የምክር ቤቱ ምክትል ዋና ጸሐፊ አቶ ጸደቀ ድጋፌ ምክር ቤቱ ከሚሠራቸው ተግባራት አንዱ የግሉ ዘርፍ በአህጉርና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ እንዲሆንና ምርትና አገልግሎቶች የተሻለ ገበያ እንዲያገኙ ማድረግ መሆኑን አንስተዋል።



ሥለሆነም በአፍሪካ ነጻ የንግድ ቀጣና ሥምምነት ትግበራ ዙሪያ የተዘጋጀው ሥልጠናም በአፍሪካ ካለው ገበያ የሚገኘውን እድል በአግባቡ ለመጠቀምና ተወዳዳሪ ለመሆን ግንዛቤን ለማሣደግ የተዘጋጀ መሆኑን ገልጸዋል።



ሥልጠናውም የኢትዮጵያ ቢዝነሶች የተሻለ ዝግጁ እንዲሆኑ ግንዛቤ እንዲኖራቸው በማሥቻል የላቀ ሚና እንደሚኖረው ይጠበቃል።

**የኢትዮጵያ ደን ልማት በአዳማ ከተማ ሃይሌ ሪዞርት የግሉ ዘርፍ ተሳትፎ በደን ልማት (Private Sector Engagement in Forestry) በሚል ርዕስ ያዘጋጀው ወርክሾፕ በመካሄድ ላይ ይገኛል።**

**የኢትዮጵያ ደን ልማት በአዳማ ከተማ ሃይሌ ሪዞርት የግሉ ዘርፍ ተሳትፎ በደን ልማት (Private Sector Engagement in Forestry) በሚል ርዕስ ያዘጋጀው ወርክሾፕ በመካሄድ ላይ ይገኛል።**




**በወርክሾፑ ላይ የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ም/ቤት ገለፃና ማብራሪያ አድርጓል።**



**በማብራሪያው የም/ቤቱ ኣላማ፣ እየተደረጉ ያሉ ስኬታማ የሪፎርም ስራዎችና ያጋጠሙ ተግዳሮቶች እንዲሁም በ"Forestry" ዙሪያ የተሰሩ ስራዎችና ግኝቶች ተካተዋል።**

**በተጨማሪም አብሮ በመሥራት ላይ ክፍተቶች እንዳሉ እና ለወደፊት በጋራ መስራት እንዲቻል ጥቆማ ተሰጥቷል።**

**ወርክሾፑ በም/ቤቱ እና በተለያዩ ባለድርሻ አካላት መካከል ስለሚኖረው የተሳለጠ ግንኙነት ውጤታማ ተሞክሮ እንደሚኖረው ይጠበቃል።**

# ሐምሌ 5 "በመትከል ማንሰራራት”




# የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት








# የግሉ ዘርፍ ድምጽ!



**የንግድ ምክርቤቱ ራዕይ ፣ተልዕኮ ፣ እሴቶች እና ቀዳሚ ስትራቴጂካዊ አምዶች**

## ራዕይ

"በግሉ ዘርፍ የሚመራ ኢኮኖሚና አካታች ዕድገት በሁለት የስትራቴጂክ ዘመናት ውስጥ እውን ሆኖ ማየት"

## ተልዕኮ

"የኢትዮጵያን የግል ዘርፍ በመወከል፣ በመደገፍና ለመብትና ጥቅሙ አድቮኬት በማድረግ፤ ንግድን፣ ኢንቨስትመንትንና ፈጠራን በማስተዋወቅና በማበረታታት አካታች ኢኮኖሚያዊ ዕድገትና ብልፅግናን ማምጣት"

## ዕሴቶች

- ታማኝነት
- ሙያዊ ብቃት
- አባላት ተኮር ምላሽ ሰጪነት
- ትብብራዊ ጥምረት
- ግልፅነት
- ተጠያቂነት
- ማህበራዊ ኃላፊነት

## ቀዳሚ ስትራቴጂካዊ ጉዳዮች (ስትራቴጂካዊ አምዶች)

1. አድቮኬሲና የፖሊሲ ተፅዕኖ
2. ጠንካራ የአባላት ተሳትፎና ድጋፍ
3. የሀብት ማሰባሰብና በአግባቡ መጠቀም
4. የአቅም ግንባታና ሥርዓት ማሻሻያ
5. ቴክኖሎጂን ማካተት እና ዲጂታል ሽግግር
6. ዘላቂነት ያለው ማኅበራዊ ኃላፊነት
7. ንግድና ኢንቨስትመንት ማስፋፋት
8. ሁሉን-አቀፍ ጉዳዮች (Cross-cutting issues)


ዋና አዘጋጅ:-

**ተሾመ ዋቅጂራ**

ም/ዋና አዘጋጅ:-

**ደበበ አበበ**

አዘጋጅ

**ስማቸው ተበጀ**

ፎቶግራፍ

**ያለምፍሬ በቀለ**



The Ethiopian Chamber of Commerce and Secoral Associations (ECCSA)

ስልክ: +251115514005

ፋክስ: + 251115517699

P. O. Box 517,

ኢ-ሜይል: info@ethiopianchamber.com

ድረ ገጽ: www.ethiopianchamber.com

ቴሌግራም t.me/ethiopiachamber

ትዊተር https://twitter.com/EthiopiaChamber

ፌስ ቡክ: https://www.facebook.com/EthiopianChamber

Youtube: https://www.youtube.com/channel/UCMEZ4TO8dQiIJvk2IQkTxhA

Linkedin(ሊንክዲን):https://www.linkedin.com/company/ethiopianchamber/in